**መሢሁ ማን ነው?** ከብሉይ ኪዳን (ታናህ) የተወሰዱ70 አበይት ጥቅሶች...

እነዚህ: ቀናት: **ለመሢሁ**: መወለድ: የምጥ :ቀናት: እንደሆኑ: ታውቃላችሁ:-ነገር :ግን: መሢሁ :ማን: እንደሆነ: ታውቃላችሁን? እቺ :ትንሽ: መጽሐፍ: ሥለ: መሢሁ: ከብሉይ: ኪዳን:"**ከታናህ**":ወይም:**ከይሁዳውያን ቅዱሥ መጻሕፍት* (ህገ ኦሪት:ነቢያተና:መጻሕፍት:)** ብቻ:የተወሰዱ :70 :ትንቢታዊ: ጥቅሶችን: ታካትታለች::
**አንቡት!** እነዚህ : ጥቅሶች: **እውነተኛው: የእሥራዔልን: መሢህ** :በግልፅ ያስረዱናል

**ትንቢተ ኢሳይያስ 9:6,7**

6 **ሕፃን** ተወልዶልናልና፥ **ወንድ ልጅም** ተሰጥቶናልና **አለቅነትም በጫንቃው** ላይ ይሆናል ስሙም **ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ** ተብሎ ይጠራል።

7 ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ **በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፥ ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም**። **የእግዚአብሔር ቅንዓት** ይህን ያደርጋል።

**ትንቢተ ሚክያስ 5:2,4**

2 አንቺም **ቤተ ልሔም ኤፍራታ** ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ **ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን** ይወጣልኛል።
ትንቢተ ሚክያስ 5:4
4 እርሱም ይቆማል፥ **በእግዚአብሔርም ኃይል በአምላኩ በእግዚአብሔር ስም ግርማ መንጋውን ይጠብቃል** እነርሱም ይኖራሉ እርሱ አሁን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ **ታላቅ** ይሆናልና።

**ኦሪት ዘፍጥረት 18:13,14**

13 **እግዚአብሔርም አብርሃምን** አለው። ካረጀሁ በኋላ በውኑ እወልዳለሁን? ስትል ሣራ ለምን ሳቀች?

14 **በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?** የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ እመለሳለሁ ሣራም **ልጅን** ታገኛለች።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 7:14**
14 ስለዚህ **ጌታ** ራሱ **ምልክት** ይሰጣችኋል እነሆ፥ **ድንግል ትፀንሳለች**፥ **ወንድ ልጅም** ትወልዳለች፥ ስሙንም **አማኑኤል** (**እግዚአብሄር ከእኛ ጋር**) ብላ ትጠራዋለች። **[መሢሁ ]**

**ትንቢተ ዘካርያስ 12:10 (ለተጨማሪ ማብራሪያመዝሙረ ዳዊት 27:7-22) [ መሢሁ!]**
10 በዳዊትም ቤት ላይ፥ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ፥ የሞገስንና የልመናን መንፈስ አፈስሳለሁ **ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ** ሰውም **ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል**፥ ሰውም ለበኩር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኀዘን ያዝኑለታል።

**ትንቢተ ዳንኤል 7:9,13,14**
9 **ዙፋኖችም** እስኪዘረጉ ድረስ አየሁ፥ **በዘመናት የሸመገለውም** ተቀመጠ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ፥ የራሱም ጠጕር እንደ ጥሩ ጥጥ ነበረ ዙፋኑም የእሳት ነበልባል ነበረ፥ መንኰራኵሮቹም
የሚነድድ እሳት ነበሩ።

13 በሌሊት ራእይ አየሁ እነሆም፥ **የሰው ልጅ** የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ **በዘመናት ወደ ሸመገለውም** ደረሰ ወደ ፊቱም አቀረቡት።

14 ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፥ **የመንግሥቱም ማይጠፋ ነው።**

**ኦሪት ዘፍጥረት 49:10 (ለተጨማሪ ማብራሪያኦሪት ዘኍልቍ24:17)** [ **መሢሁ!**]
10 በትረ መንግሥት **ከይሁዳ** አይጠፋም፥ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፥ **ገዥ** የሆነው እስኪመጣ ድረስ
የአሕዛብ መታዘዝም ለእርሱ ይሆናል።

**ትንቢተ ዳንኤል9:26**
26 ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ **መሢሕ ይገደላል፥** በእርሱም ዘንድ ምንም የለም የሚመጣውም
አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ ፍጻሜውም በጐርፍ ይሆናል፥ እስከ መጨረሻም ድረስ
ጦርነት ይሆናል ጥፋትም ተቀጥሮአል።

**ትንቢተ ዳንኤል 3:24,25**

24 የዚያን ጊዜም ንጉሡ ናቡከደነፆር ተደነቀ ፈጥኖም ተነሣ አማካሪዎቹንም። ሦስት ሰዎች አስረን
በእሳት ውስጥ ጥለን አልነበረምን? ብሎ ተናገራቸው። እርሱም፦ ንጉሥ ሆይ፥ እውነት ነው ብለው
ለንጉሡ መለሱለት።

25 እርሱም፦ እነሆ፥ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ ምንም
አላቈሰላቸውም **የአራተኛውም መልክ የአማልክትን ልጅ ይመስላል** ብሎ መለሰ።

**መዝሙረ ዳዊት 110:1** (በንጉሥ ዳዊት የተፃፈ)
1 **እግዚአብሔር ጌታዬን፦** ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ **በቀኜ ተቀመጥ አለው።**

**መጽሐፈ ምሳሌ 30:4**
4 ወደ ሰማይ የወጣ የወረደስ ማን ነው? ነፋስንስ በእጁ የጨበጠ ማን ነው? ውኃንስ በልብሱ የቋጠረ ማን
ነው? የምድርን ዳርቻ ሁሉ ያጸና ማን ነው? ይህን ታውቅ እንደ ሆንህ፥ **ስሙ ማን የልጁስ ስም ማን ነው?**

**ኦሪት ዘዳግም 18:15,18,19** [ **መሢሁ!**]
15 አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ **ነቢይ** ያስነሣልሃል እርሱንም
ታደምጣለህ።

18 ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፥
ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል

19 በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 59:16,17,20** (ትንቢተ ኢሳይያስ63:5,6, ትንቢተ ሕዝቅኤል 22:30 ተጨማሪ ማብራሪያ) [
**መሢሁ!**]

16 ሰውም እንደሌለ አየ (**እግዚአብሔር** )፥ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም ስለዚህ **የገዛ
ክንዱ መድኃኒት አመጣለት፥** ጽድቁም አገዘው።

17 **ጽድቅንም እንደ ጥሩር ለበሰ፥** በራሱም ላይ የማዳንን ራስ ቍር አደረገ የበቀልንም ልብስ ለበሰ፥
በቅንዓትም መጐናጸፊያ ተጐናጸፈ።
20 **ለጽዮን ታዳጊ ይመጣል፥** በያዕቆብም ዘንድ ከኃጢአት ለሚርቁ፥ ይላል እግዚአብሔር፦

**መዝሙረ ዳዊት 40:7,8,9**

7 በዚያን ጊዜ አልሁ። **እነሆ፥ መጣሁ ስለ እኔ በመጽሐፍ ራስ ተጽፎአል**

8 አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ፥ **ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው።**

9 በታላቅ ጉባኤ **ጽድቅን አወራሁ** እነሆ፥ ከንፈሮቼን አልከለክልም አቤቱ፥ አንተ ጽድቄን ታውቃለህ

**ትንቢተ ኢሳይያስ 52:10,13-15**

10 እግዚአብሔር **የተቀደሰውን ክንዱን** በአሕዛብ ሁሉ ፊት ገልጦአል፥ በምድር ዳርቻ የሚኖሩትም ሁሉ
የአምላካችንን መድኃኒት ያያሉ።

13 እነሆ፥ **ባሪያዬ** በማስተዋል ያደርጋል ይከብራል ከፍ ከፍም ይላል፥ እጅግ ታላቅም ይሆናል።

14 ፊቱ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ፥ መልኩም ከሰዎች ልጆች ይልቅ ተጎሳቍሎአልና ብዙ ሰዎች ስለ አንተ
እንደ ተደነቁ፥ እንዲሁ **ብዙ አሕዛብን ያስደንቃል (በደሙ)**

15 ያልተነገረላቸውንም ያያሉና፥ ያልሰሙትንም ያስተውላሉና ነገሥታት ስለ እርሱ አፋቸውን ይዘጋሉ።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 53:1,4-6,11** (ለተጨማሪ ማብራሪያ መዝሙረ ዳዊት 98:1-3)

1 የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል? **የእግዚአብሔርስ ክንድ** ለማን ተገልጦአል?

4 በእውነት **ደዌያችንን ተቀበለ** ሕመማችንንም ተሸክሞአል እኛ ግን እንደ ተመታ
በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው።

5 እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ
ነበረ፥ **በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።**

6 እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ
**እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።**

11 ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥
ኃጢአታቸውን ይሸከማል።

**መዝሙረ ዳዊት 22:1,16** [ *መሢሁ!*]

1 **አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ?** እኔን ከማዳንና ከጩኸቴ ቃል ሩቅ ነህ።

16 ብዙ ውሾች ከብበውኛልና የክፋተኞች ጉባኤም ያዘኝ **እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ።**

**ትንቢተ ዘካርያስ 9:9-11** [ *መሢሁ!*]

9 አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እጅግ ደስ ይበልሽ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፥ እልል በዪ እነሆ፥
**ንጉሥሽ** ጻድቅና አዳኝ ነው ትሑትም ሆኖ በአህያም፥ በአህያይቱ ግልገል በውርጫይቱ ላይ
ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል።

10 ሰረገላውንም ከኤፍሬም ፈረሱንም ከኢየሩሳሌም አጠፋለሁ የሰልፉም ቀስት ይሰበራል፥
ለአሕዛብም ሰላምን ይናገራል ግዛቱም ከባሕር እስከ ባሕር፥ ከወንዙም እስከ ምድር ዳርቻ
ድርስ ይሆናል።

11 **ለአንቺም ደግሞ ስለ ቃል ኪዳንሽ ደም፥** እስሮችሽን ውኃ ከሌለበት ጉድጓድ አውጥቻለሁ።

**ትንቢተ ኤርምያስ 31:31-34**

31 እነሆ፥ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር **አዲስ ቃል ኪዳን** የምገባበት ወራት
ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር

32 ከግብጽ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ
ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥ እኔም ቸል አልኋቸው፥ ይላል
እግዚአብሔር፡-

33 ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና፥ ይላል
እግዚአብሔር ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ **በልባቸውም እጽፈዋለሁ** እኔም አምላክ
እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል።

34 እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም ወንድሙን፡- እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ
አያስተምርም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ **ሁሉ ያውቁኛልና**፥ ይላል እግዚአብሔር፡-
በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና።

**ኦሪት ዘፍጥረት 3:15** [ *መሢሁ!*]

15 በአንተና **በሴቲቱ** መካከል፥ በዘርህና **በዘርዋም** መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ
**ራስህን ይቀጠቅጣል፥** አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።

**ኦሪት ዘሌዋውያን 17:11**

11 የሥጋ ሕይወት **በደሙ** ውስጥ ነውና **ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና** በመሠዊያው
ላይ **ለነፍሳችሁ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት።**

**ትንቢተ ሕዝቅኤል 36:25-28** (ትንቢተ ሕዝቅኤል 11:19,20,16:60, 18:31,32ለተጨማሪ
ማብራሪያ)

25 ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ፥ ከርኵሰታችሁም ሁሉ
ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ።

26 **አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ** አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ የድንጋዩንም ልብ
ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ።

27 **መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም አስሄዳችኋለሁ፥** ፍርዴንም
ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ።

28 ለአባቶቻችሁም በሰጠኋት ምድር ትኖራላችሁ ሕዝብም ትሆኑኛላችሁ እኔም አምላክ
እሆናችኋለሁ።

**መዝሙረ ዳዊት 118:22-26**

22 ግንበኞች የናቁት **ድንጋይ**፥ እርሱ **የማዕዘን ራስ** ሆነ፥

23 ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፥ ለዓይናችንም ድንቅ ናት።

24 እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት ሐሤትን እናድርግ፥ በእርስዋም ደስ ይበለን።

25 አቤቱ፥ እባክህ፥ አሁን አድን አቤቱ፥ እባክህ፥ አሁን አቅና።

26 **በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው** ከእግዚአብሔር ቤት መረቅናችሁ።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 63:8-10**

8 እርሱም፡- በእውነት ሕዝቤ፥ ሐሰትን የማያደርጉ ልጆች፥ ናቸው አለ መድኃኒትም
ሆነላቸው።

9 በጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፥ የፊቱም መልአክ አዳናቸው በፍቅሩና በርኅራኄውም
ተቤዣቸው፥ በቀደመውም ዘመን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው።

10 እነርሱ ግን ዐመፁ ቅዱስ መንፈሱንም አስመረሩ ስለዚህ ተመልሶ ጠላት ሆናቸው፥
እርሱም ተዋጋቸው።

**ትንቢተ ዘካርያስ 13:7-9 [ *መሢሁ!*]**

7 ሰይፍ ሆይ፥ ባልንጀራዬ በሆነው ሰው **በእረኛዬ** ላይ ንቃ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ
እግዚአብሔር **እረኛውን ምታ፥** በጎቹም ይበተናሉ እጄንም በታናናሾች ላይ እመልሳለሁ።

8 በምድርም ሁሉ ላይ ሁለት ክፍል ተቈርጠው ይሞታሉ፥ ይላል እግዚአብሔር
ሦስተኛውም ክፍል በእርስዋ ውስጥ ይቀራል።
9 **ሦስተኛውንም ክፍል ወደ እሳት አገባለሁ፥** ብርም እንደሚነጥር አነጥራቸዋለሁ፥ ወርቅም
እንደሚፈተን እፈትናቸዋለሁ እነርሱም ስሜን ይጠራሉ፥ እኔም እሰማቸዋለሁ እኔም። ይህ
ሕዝቤ ነው እላለሁ እርሱም፡- እግዚአብሔር አምላኬ ነው ይላል።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 42:1-4,6,7 [ *መሢሁ!*]**

1 እነሆ ደግፌ የያዝሁት **ባሪያዬ** ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት **ምርጤ** በእርሱ ላይ **መንፈሴን**
አድርጌአለሁ፥ እርሱም ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል።

2 አይጮኽም ቃሉንም አያነሣም፥ ድምፁንም በሜዳ አያሰማም።

3 የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፥ የሚጤሰንም ክር አያጠፋም በእውነት ፍርድን
ያወጣል።

4 በምድርም ፍርድን እስኪያደርግ ድረስ ይበራል እንጂ አይጠፋም አሕዛብም በስሙ
ይታመናሉ።
6- እኔ እግዚአብሔር **በጽድቅ ጠርቼሃለሁ፥ እጅህንም እይዛለሁ** እጠብቅህማለሁ፥
7- የዕውሩንም ዓይን ትከፍት ዘንድ የተጋዘውንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን
ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ **ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን** አድርጌ እሰጥሃለሁ።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 49:5-9 ( ትንቢተ ኢሳይያስ 11:10አንብቡት) [ *መሢሁ!*]**

5 አሁንም በእግዚአብሔር ዓይን ከብሬአለሁና፥ **አምላኬም ጉልበት ሆኖኛልና** ያዕቆብን
ወደ እርሱ እንድመልስ እስራኤልንም ወደ እርሱ እንድሰበስብ **ባሪያ እሆነው ዘንድ**
ከማኅፀን ጀምሮ የሠራኝ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።

6 እርሱም፡- የያዕቆብን ነገዶች እንድታስነሣ ከእስራኤልም የዳኑትን እንድትመስል **ባሪያዬ
ትሆን ዘንድ** እጅግ ቀላል ነገር ነውና እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ
ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ይላል።

7 የእስራኤል ታዳጊ ቅዱሱም፥ እግዚአብሔር፥ ሰዎች ለሚንቁት ሕዝብም ለሚጠላው
ለገዥዎች ባሪያ እንዲህ ይላል። ስለ ታማኙ ስለ እግዚአብሔር ስለ መረጠህም ስለ
እስራኤል ቅዱስ ነገሥታት አይተው ይነሣሉ፥ መሳፍንትም አይተው ይሰግዳሉ።

8 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በተወደደ ጊዜ ሰምቼሃለሁ፥ **በመድኃኒትም ቀን**
ረድቼሃለሁ እጠብቅህማለሁ፥ ምድርንም ታቀና ዘንድ፥ ውድማ የሆኑትንም ርስቶች
ታወርስ ዘንድ፥

9 የተጋዙትንም። ውጡ በጨለማም የተቀመጡትን፡- ተገለጡ ትል ዘንድ **ቃል ኪዳን
አድርጌ ለሕዝቡ ሰጥቼሃለሁ።** በመንገድም ላይ ይሰማራሉ፥ ማሰማርያቸውም በወና
ኮረብታ ሁሉ ላይ ይሆናል።

**ትንቢተ ዘካርያስ 3:6,8,9,(ትንቢተ ዘካርያስ 3:1-4አንብቡት)**
6 **የእግዚአብሔርም መልአክ** በኢያሱ እንዲህ ሲል አዳኘበት።

8 **ታላቁ ካህን** ኢያሱ ሆይ፥ ስማ በፊትህም የሚቀመጡት ባልንጀሮችህ ለምልክት
የሚሆኑ ሰዎች ናቸውና ይስሙ እነሆ፥ **እኔ ባሪያዬን ቍጥቋጥ አወጣለሁ።**

9 በኢያሱ ፊት ያኖርሁት ድንጋይ እነሆ አለ በአንዱ ድንጋይ ላይ ሰባት ዓይኖች አሉ
እነሆ፥ ቅርጹን እቀርጻለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ የዚያችንም ምድር
በደል **በአንድ ቀን** አስወግዳለሁ።[ **መሢሁ!**]

**ትንቢተ ዘካርያስ 6:11,12,13(ታላቁ ካህን ኢያሱ በመጽሐፈ ዕዝራ 3:2 ያበራራዋል)**

11 ብርንና ወርቅን ከእነርሱ ውሰድ፥ **አክሊሎችንም ሥራ** በታላቁም ካህን በኢዮሴዴቅ
ልጅ በኢያሱ ራስ ላይ ድፋቸው፥

12 እንዲህም በለው። የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ ስሙ
**ቍጥቋጥ** የሚባል ሰው በስፍራው ይበቅላል፥ የእግዚአብሔርንም መቅደስ ይሠራል።

13 እርሱ የእግዚአብሔርን መቅደስ ይሠራል፥ ክብርንም ይሸከማል፥ **በዙፋኑም ላይ
ተቀምጦ ይነግሣል በዙፋኑም ላይ ካህን ይሆናል፥** የሰላምም ምክር በሁለቱ መካከል
ይሆናል።የንጉሥ ካህን! [ **መሢሁ!**]

**ኦሪት ዘፍጥረት 22:8,10-14,15-18(ኦሪት ዘፍጥረት18:1,2,10,16-18,22ማየት ይቻላል )**
8 አብርሃምም፦ **ልጄ** ሆይ፥ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው ሁለቱም
አብረው ሄዱ።

10 አብርሃምም እጁን ዘረጋ፥ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሣ።

11 **የእግዚአብሔር መልአክም** ከሰማይ ጠራና። አብርሃም አብርሃም አለው

12 እርሱም፦ እነሆኝ አለ። እርሱም፦ በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥ አንዳችም
አታድርግበት አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ
ሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ።

13 አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ
ሳቤቅ ተይዞ አየ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት
አድርጎ ሠዋው።

14 አብርሃምም ያንን ቦታ ያህዌ ይርኤ ብሎ ጠራው እስከ ዛሬም ድረስ
በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል ይባላል

15 የእግዚአብሔር መልአክም አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው፥

16 እንዲህም አለው፦ **እግዚአብሔር፦ በራሴ ማልሁ** ይላል ይህን ነገር አድርገሃልና፥
አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና

17 በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፥ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር
እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ **ዘርህም**[ **መሢሁ!**]  የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል

18 የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፥ ቃሌን ሰምተሃልና።

**መዝሙረ ዳዊት 2:6,7,12**

6 **እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ።**

7 ትእዛዙን እናገራለሁ እግዚአብሔር አለኝ። **አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ።**

12 ተግሣጹን ተቀበሉ ጌታ እንዳይቈጣ እናንተም በመንገድ እንዳትጠፉ፥ ቍጣው ፈጥና
ትነድዳለችና። በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው።

**ኦሪት ዘፍጥረት 14:18-20** [ ***መሢሁ!*** ]

18 **እንየሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም ጀራንና የወይን ጠጅን** አወጣ እርሱም **የልዑል እግዚአብሔር ካህን** ነበረ።

19 ባረከውም። አብራም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው

20 ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው አለውም። አብራምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው።

**ኦሪት ዘፍጥረት 32:24,28,30(ትንቢተ ሆሴዕ 13:4 ማየት ይቻላል...ከእኔም በቀር ሌላ መድኃኒት የለም።)**
24 ያዕቆብ ግን ለብቻው ቀረ **አንድ ሰውም** እስከ ንጋት ድረስ ይታገለው ነበር።
28 አለውም፡- ከእንግዲህ ወዲህ **ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ** አይባል **ከእግዚአብሔር** ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና።
30 ያዕቆብም። **እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፥** ሰውነቴም ድና ቀረች ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው።[ ***መሢሁ!*** ]

**ኦሪት ዘጸአት 3:2-6** [ ***መሢሁ!*** ]

2 **የእግዚአብሔርም መልአክ** በእሳት ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ መካከል ታየው እነሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ።

3 ሙሴም፡- ልሂድና ቍጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ።

4 እግዚአብሔር እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ **እግዚአብሔር ከቍጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ።** ሙሴ፥ ሙሴ ሆይ አለ።

5 እርሱም፡- እነሆኝ አለ። ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው።

6 ደግሞም፡- **እኔ የአባትህ አምላክ፥** የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ።

**ኦሪት ዘጸአት 23:20-23** [ ***መሢሁ!*** ]

20 በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ፥ እነሆ፥ **እኔ መልአከን በፊትህ** እሰድዳለሁ።

21 **በፊቱ ተጠንቀቁ፥ ቃሉንም አድምጡ ስሜም በእርሱ ስለ** ሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና **አታስመርሩት።**

22 **አንተ ግን ቃሉን ብትሰማ፥** ያልሁህንም ሁሉ ብታደርግ፥ ጠላቶችህን እጣላቸዋለሁ፥ የሚያስጨንቁህንም አስጨንቃቸዋለሁ።

23 **መልአኬ በፊትህ ይሄዳልና፥** ወደ አሞራውያንም ወደ ኬጢያውያንም ወደ ፌርዛውያንም ወደ ከነዓናውያንም ወደ ኤዊያውያንም ወደ ኢያቡሳውያንም ያገባሃል እኔም አጠፋቸዋለሁ።

**መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 5:13-15** [ ***መሢሁ!***]

13 እንዲህም ሆነ፤ ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ ዓይኑን አንሥቶ ተመለከተ፥ እነሆም፥
የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ ነበር፤ ኢያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ። ከእኛ
ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን? አለው።

14 እርሱም፦ አይደለሁም፤ እኔ ***የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ*** ሆኜ አሁን
መጥቼአለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ **ሰገደና። ጌታዬ** ለባሪያው
የሚነግረው ምንድር ነው? አለው።

15 ***የእግዚአብሔርም ሠራዊት አለቃ*** ኢያሱን። አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና
ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ።

***መጽሐፈ መሣፍንት*** **13:3,18,20,22** [ ***መሢሁ!***]

3 **የእግዚአብሔርም መልአክ** ለሴቲቱ ተገልጦ እንዲህ አላት፦ እነሆ፥ አንቺ መካን ነሽ፥
ልጅም አልወለድሽም ነገር ግን ትፀንሻለሽ፥ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ።

18 **የእግዚአብሔርም መልአክ። ስሜ ድንቅ ነውና** ለምን ትጠይቃለህ? አለው።

19 ማኑሄም የፍየሉን ጠቦትና የእህሉን ቍርባን ወስዶ በድንጋይ ላይ ለእግዚአብሔር
አቀረበው። **መልአኩም** ተአምራት አደረገ፥ ማኑሄና ሚስቱም ይመለከቱ ነበር።

20 ነበልባሉም ከመሠዊያው ላይ ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ የእግዚአብሔርም መልአክ
በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ዐረገ ማኑሄና ሚስቱም ተመለከቱ፥ በምድርም
በግምባራቸው ተደፉ።

22 ማኑሄም ሚስቱን፦ **እግዚአብሔርን አይተናልና** ሞት እንሞታለን አላት።(ትንቢተ
ኢሳይያስ 9:6 ማየት ይቻላል)

**ትንቢተ ኤርምያስ 23:5,6**

5 **እነሆ፥ ለዳዊት ጻድቅ ቍጥቋጥ** የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ **ይላል እግዚአብሔር፥**
እርሱም **እንደ ንጉሥ ይነግሣል፥** ይከናወንለታልም፥ በምድርም ፍርድንና ጽድቅን
ያደርጋል።

6 በዘመኑም ይሁዳ ይድናል እስራኤልም ተዘልሎ ይቀመጣል፥ የሚጠራበትም ስም።
**እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው።**

**ትንቢተ ኤርምያስ 33:14-18** [ ***መሢሁ!***]

14 እነሆ፥ ስለ እስራኤል ቤትና ስለ ይሁዳ ቤት **የተናገርሁትን መልካም ቃል**
የምፈጽምበት ዘመን ይመጣል፥ **ይላል እግዚአብሔር፦**

15 በዚያም ዘመን በዚያም ጊዜ ለዳዊት **የጽድቅን ቍጥቋጥ አበቅልለታለሁ እርሱም**
ፍርድንና ጽድቅን በምድር ያደርጋል።

16 በዚያም ዘመን ይሁዳ ይድናል ኢየሩሳሌምም ተዘልላ ትቀመጣለች
የምትጠራበትም ስም። **እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው።**

17 እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። በእስራኤል ቤት ዙፋን ላይ የሚቀመጥ ሰው
ከዳዊት ዘንድ አይታጣም

18 የሚቃጠለውንም መሥዋዕት የሚያቀርብ የእህሉንም ቍርባን የሚያቃጥል
**ሁልጊዜም የሚሠዋ ሰው** ከሌዋውያን ካህናት ዘንድ **በእኔ ፊት አይታጣም።**
**[መሢሁ የንጉሥ ካህን የንጉሥ ዳዊትና የካህኑ የፃዶቅ ዘር ነው]**

**ትንቢተ ዘካርያስ 9:14,15,16(በተጨማሪ እነዚህን ጥቅሶች ማየት ይቻላል ትንቢተ ኢሳይያስ 27:13 ) [ *መሢሁ!*]**

14 **እግዚአብሔርም** በእነርሱ ላይ ይገለጣል፥ ፍላጻውም እንደ መብረቅ ይወጣል **ጌታ እግዚአብሔርም መለከትን ይነፋል**፥ በደቡብም ዐውሎ ነፋስ ይሄዳል።

15 የሠራዊት **ጌታ እግዚአብሔር** ይጠብቃቸዋል እነርሱም ይበሉአቸዋል፥
የወንጭፉንም ድንጋዮች ይረግጣሉ እንደ ወይን ጠጅም ይጠጡአቸዋል፥ እንደ
ጥዋዎችም እንደ መሠዊያም ማዕዘኖች የተሞሉ ይሆናሉ።

16 **በዚያም ቀን አምላካቸው እግዚአብሔር** እንደ ሕዝቡ መንጋ ያድናቸዋል እነርሱም
ለአክሊል እንደሚሆኑ እንደ ከበሩ ድንጋዮች ይሆናሉ፥ በምድሩም ላይ
ይብለጨለጫሉ።

***መሙረ ዳዊት* 24:7-10 [ *መሢሁ!*]**

7 እናንት መኳንንቶች፥ በሮችን ክፈቱ፥ የዘላለም ደጆችም ይከፈቱ፥ **የክብርም ንጉሥ**
ይግባ።

8 ይህ **የክብር ንጉሥ ማን ነው?** እግዚአብሔር ነው፥ ብርቱና ኃያል፥ እግዚአብሔር
ነው፥ በሰልፍ ኃያል።

9 እናንተ መኳንንቶች፥ በሮችን ክፈቱ፥ የዘላለም ደጆችም ይከፈቱ፥ **የክብርም ንጉሥ**
ይግባ።

10 ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው? **የጭፍሮች አምላክ እግዚአብሔር፥ እርሱ
የክብር ንጉሥ ነው።**

**ትንቢተ ኢሳይያስ 16:5**

5 **ዙፋንም** በምሕረት ይቀናል፥ **በዚያም ላይ በዳዊት ድንኳን** ፍርድን የሚሻ ጽድቅንም
የሚያፈጥን **ፈራጅ [መሢሁ! የንጉሥ ካህን]** በእውነት ይቀመጣል

**ትንቢተ ዳንኤል 10:5,6,14,21**

5 እነሆም፥ በፍታ የለበሰውን ጥሩም የአፌዝን ወርቅ በወገቡ ላይ የታጠቀውን **ሰው**
አየሁ።

6 አካሉም እንደ ቢረሌ ይመስል ነበር፥ **ፊቱም እንደ መብረቅ ምስያ ነበረ፥ ዓይኖቹም
እንደሚንበለበል ፋና፥** ክንዶቹና እግሮቹም እንደ ጋለ ናስ፥ **የቃሉም ድምፅ [መሢሁ!]**
]እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ነበረ።

14 ራእዩም ገና ለብዙ ዘመን ነውና በኋለኛው ዘመን ለሕዝብህ የሚሆነውን አስታውቅህ
ዘንድ አሁን መጥቻለሁ።
21 ነገር ግን **በእውነት ጽሑፍ የተጻፈውን** እነግርሃለሁ በዚህም ነገር ከአለቃችሁ
ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያጸናኝ የለም።

**ትንቢተ ዳንኤል 12:6,7**

6 አንዱም ከወንዙ ውኃ በላይ የነበረውን **በፍታም የለበሰውን**፦ የዚህ ድንቅ ፍጻሜ
እስከ መቼ ነው? አለው።

7 ከወንዙም ውኃ በላይ የነበረው በፍታም የለበሰው ሰው ቀኙና ግራ እጁን ወደ
ሰማይ አንሥቶ። **ለዘመንና ለዘመናት ለዘመንም እኩሌታ ነው የተቀደሰውም ሕዝብ
ኃይል መበተን በተጨረሰ ጊዜ** ይህ ሁሉ ይፈጸማል ብሎ ለዘላለም ሕያው ሆኖ
በሚኖረው ሲምል ሰማሁ።
(በተጨማሪ እነዚህን ጥቅሶች ማየት ይቻላል ኦሪት ዘዳግም 32:39-41) [ *መሢሁ!*]

**ትንቢተ ኢሳይያስ 11:1,2,4,5 (በተጨማሪ ትንቢተኢሳይያስ 61:1-3) [ መሢሁ!]**

1 ከእሴይ ግንድ **በትር** ይወጣል፥ ከሥሩም **ቍጥቋጥ** ያፈራል።

2 **የእግዚአብሔር መንፈስ፥ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፥ የምክርና የኃይል**
**መንፈስ፥ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል።**

4 ነገር ግን ለድሆች በጽድቅ ይፈርዳል፥ ለምድርም የዋሆች በቅንነት ይበይናል
በአፉም በትር ምድርን ይመታል፥ **በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል።**

5 የወገቡ መታጠቂያ ጽድቅ፥ የጎኑም መቀነት **ታማኝነት ይሆናል።**

**መዝሙረ ዳዊት 89:20,21 ,26-29,35,36(ተጨማሪ ማየት 3,4,34,37) [ መሢሁ!]**

20 **ባሪያዬን ዳዊትን** አገኘሁት፥ ቅዱስ ዘይትም ቀባሁት።

21 እጄም ትረዳዋለች፥ ክንዴም ታጸናዋለች።

26 እርሱ። **አባቴ አንተ ነህ፥ አምላኬ የመድኃኒቴም** መጠጊያ ይላል።

27 እኔም ደግሞ **በኵሬ** አደርገዋለሁ፥ **ከምድር ነገሥታትም ከፍ ይላል።**

28 ለዘላለምም ምሕረቴን ለእርሱ እጠብቃለሁ፥ ኪዳኔም በእርሱ ዘንድ የታመነ
ነው።

29 **ዘሩንም**[ መሢሁ!] ለዓለምና **ለዘላለም፥ ዙፋኑንም** እንደ ሰማይ ዘመን
አደርጋለሁ።

35 ዳዊትን እንዳልዋሸው አንድ ጊዜ በቅዱስነቴ ማልሁ።

36 **ዘሩ ለዘላለም፥** ዙፋኑም በፊቴ እንደ ፀሐይ ይኖራል።

**መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 17:10-15 ( መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 7:5,12-16)**

10 ለሕዝቤም ለእስራኤል ስፍራ አደርግለታለሁ፥ እተክለውማለሁ፥ በስፍራውም
ይቀመጣል፥ ከዚያም በኋላ አይናወጥም እንደቀድሞው ዘመንና በሕዝቤም
በእስራኤል ላይ ፈራጆች እንዳስነሣሁበት ጊዜ ግፈኞች ተመልሰው
አያስጨንቁትም ጠላቶችህንም ሁሉ አዋርዳቸዋለሁ። እግዚአብሔር ደግሞ ቤት
እንዲሠራልህ እነግርሃለሁ።

11 ወደ አባቶችህም ትሄድ ዘንድ ዕድሜህ በተፈጸመ ጊዜ ከልጆችህ የሚሆነውን
**ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ** መንግሥቱንም አጸናለሁ።

12 **እርሱ ቤት ይሠራልኛል ዙፋኑንም ለዘላለም አጸናለሁ።**

13 እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል ከአንተ አስቀድሞ ከነበረው
እንዳራቅሁ፥ ምሕረቴን ከእርሱ አላርቅም።

14 **በቤቴና በመንግሥቴም ለዘላለም አቆመዋለሁ ዙፋኑም ለዘላለም**
**ይጸናል።**

15 እንደዚህ ነገር ሁሉ እንደዚህም ራእይ ሁሉ ናታን ለዳዊት ነገረው።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 53፥1-12** [ *መሢሁ!*]

1 የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል? **የእግዚአብሔርስ ክንድ** ለማን
ተገልጦአል?

2 በፊቱ እንደ ቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አድጎአል። መልክና ውበት
የለውም፥ ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም።

3 የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው ሰውም
ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፥ እኛም አላከበርነውም።

4 በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል እኛ ግን እንደ
ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው።

5 እርሱ ግን **ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥** ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም
ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ **በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን!**

6 እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ
መንገዱ አዘነበለ **እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።**

7 **ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም** ለመታረድ እንደሚነዳ **ጠቦት፥**
በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል **በግ፥** እንዲሁ አፉን አልከፈተም።

8 በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ **ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር
እንደ ተወገደ** ከትውልዱ ማን አስተዋለ?

9 ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፥ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆኖም ግፍን
አላደረገም ነበር፥ በአፉም ተንኰል አልተገንበትም ነበር።

10 እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈከደ **ነፍሱን ስለ ኃጢአት
መሥዋዕት ካደረገ በኋላ** ዘሩን ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርም
ፈቃድ በእጁ ይከናወናል።

11 **ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል** ደስም ይለዋል **ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ
ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥** ኃጢአታቸውን ይሰከማል።

12 ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፥ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል
**ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥** ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና እርሱ ግን
**የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥** ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 61፥1,2** [ *መሢሁ!*]

1 **የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥** ለድሆች የምሥራችን እሰብክ
ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፥
ለተማረኩትም ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል።

2 **የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን**
እናገር ዘንድ፥ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ

**ትንቢተ ዳንኤል 2:34,35**

34 እጅም ሳይነካው **ድንጋይ** ከተራራው ተፈንቅሎ ከብረትና ከሸክላ
የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየህ።

35 የዚያን ጊዜም ብረቱና ሸክላው፥ ናሱና ብሩ ወርቁም በአንድነት ተፈጩ፥
በመከርም ጊዜ በአውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሆነ ነፋስም ወሰደው፥
ቦታውም አልታወቀም ምስሉንም የመታ **ድንጋይ** [ ***መሢሁ!***]**ታላቅ ተራራ
ሆነ ምድርንም ፈጽሞ ሞላ**

**ትንቢተ ኢሳይያስ 28:16**

16 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ በጽዮን **ድንጋይን**
ለመሠረት አስቀምጣለሁ **የተፈተነውን፥ የከበረውን፥ መሠረቱ የጸናውን
የማዕዘን ድንጋይ** የሚያምን አያፍርም።[ ***መሢሁ!***]

**ትንቢተ ኢሳይያስ 8:14,15**

14 እርሱም **ለመቅደስ** ይሆናል ነገር ግን ለሁለቱ ለእስራኤል ቤቶች
**ለዕንቅፋት ድንጋይና ለማሰናከያ ዓለት፥** በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩ
ለወጥመድና ለአሽክላ ይሆናል።

15 ብዙዎችም በእርሱ ይሰናከላሉ፥ ይወድቁማል፥ ይሰበሩማል፥
ይጠመዱማል፥ ይያዙማል።[ ***መሢሁ!***]

**ኦሪት ዘፍጥረት 1:26**

(በተጨማሪ እነዚህን ጥቅሶች ማየት ይቻላል ኦሪት ዘፍጥረት 3:22,ኦሪት
ዘፍጥረት 11:7,ትንቢተ ኢሳይያስ 6:8,ትንቢተ ኢሳይያስ 48:16)

26 **እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን** እንደ **ምሳሌአችን** እንፍጠር
የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና **ምድርን ሁሉ፥** በምድር ላይ
የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ **ይግዙ።**

22 " እግዚአብሔር አምላክም አለ። እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ
**ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ"**

7 " **ኑ፥ እንውረድ** አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ
እንደባልቀው።"

8 " **የጌታንም ድምፅ። ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል
ሰማሁ።"**

16 "...አሁንም ጌታ **እግዚአብሔር** ና **መንፈሱ** ልከውኛል።"

***መዝሙረ ዳዊት 8:4-6***

4 ታስበው ዘንድ **ሰው ምንድር ነው?** ትጐበኘውም ዘንድ **የሰው ልጅ ምንድር ነው?**

5 **ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው** በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው።

6 በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት፥

**ትንቢተ *ሆሴዕ* 2:1**

1 የእስራኤልም ልጆች ቍጥር እንደማይሰፈርና እንደማይቈጠር እንደ ባሕር አሸዋ ይሆናል እንዲህም ይሆናል እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም ተብሎ በተነገረበት በዚያ ስፍራ "**የሕያው አምላክ ልጆች ይባላሉ!**"

***መዝሙረ ዳዊት* 82:6**

6 እኔ ግን። **አማልክት** ናችሁ፥ ሁላችሁም "**የልዑል ልጆች**" ናችሁ

**ትንቢተ ኢሳይያስ 59:1,2**

1 እነሆ፥ **የእግዚአብሔር እጅ** ከማዳን አላጠረችም፥ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም

2 ነገር ግን **በደላችሁ** በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል።

**ኦሪት ዘዳግም 24:16** (በተጨማሪ እነዚህን ጥቅሶች ማየት ይቻላልትንቢተ ሕዝቅኤል 18:4**...*ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች!***
16 አባቶች ስለ ልጆች አይገደሉ፥ ልጆችም ስለ አባቶች አይገደሉ **ነገር ግን ሁሉ እያንዳንዱ በኃጢአቱ ይገደል!**

***መዝሙረ ዳዊት* 14:3**
(በተጨማሪ *መዝሙረ ዳዊት* 53:1,*መዝሙረ ዳዊት* 53:3)
3 ***ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ*** በጎ ነገርን የሚሠራ የለም አንድም ስንኳ የለም።

**ኦሪት ዘዳግም 27:26**
26 የዚህን ሕግ ቃሎች ያደርግ ዘንድ የማያጸና **ርጉም** ይሁን ሕዝቡም ሁሉ '**አሜን!**' " ይላሉ።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 64:6** (በተጨማሪ መጽሐፈ መክብብ **7:20)**
6 **ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፥** ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም
ጨርቅ ነው ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፥ በደላችንም እንደ ነፋስ
ወስዶናል።

**ትንቢተ ሆሴዕ 5:15 [ _መሢሁ!_]**
15 **በደላቸውንም** እስኪያውቁ ድረስ፥ ፊቴንም እስኪሹ ድረስ ሄጄ ወደ
ስፍራዬ እመለሳለሁ በመከራቸው ጊዜ እጅግ አድርገው ፊቴን ይፈልጋሉ።

**ትንቢተ ዳንኤል 12:2**
(በተጨማሪ እነዚህን ጥቅሶች ማየት ይቻላል ትንቢተ ሆሴዕ 13:14,ትንቢተ
ኢሳይያስ 26:19,መጽሐፈ ኢዮብ 19:26,መዝሙረ ዳዊት 49:15)
2 በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች **_ይነቃሉ_** እኵሌቶቹ **_ወደ
ዘላለም_** ሕይወት፥ እኵሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ **_ዘላለም ጉስቍልና።_**

**ኦሪት ዘኍልቍ 23:19**(በተጨማሪ እነዚህን ጥቅሶች መጽሐፈ ሳሙኤል
ቀዳማዊ 15:29)
19 **_ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፥_** ይጸጸትም ዘንድ
የሰው ልጅ አይደለም። እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ
አይፈጽመውምን?

**ትንቢተ ኤርምያስ 31:3** (በተጨማሪ ኦሪት ዘዳግም 7:6-10,12,13)
3 እግዚአብሔርም ከሩቅ ተገለጠልኝ እንዲህም አለኝ፦ **_በዘላለም ፍቅር
ወድጄሻለሁ_** ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ።

**_*እነዚህ 70 ዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እየሱስ ክርስቶስ የእስራዔል
መሢህ መሆኑን ያረጋግጣሉ!_**

**መዝሙረ ዳዊት 138:2**
2 ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ ስለ ምሕረትህና ስለ እውነትህ
ስምህንም አመሰግናለሁ፥ በሁሉ ላይ ቅዱስ ስምህን ከፍ ከፍ
አድርገሃልና።

**መዝሙረ ዳዊት 119:89**
89 አቤቱ፥ **_ቃልህ በሰማይ ለዘላለም ይኖራል።_**

**ትንቢተ ኢሳይያስ 40:8** **እየሩሳሌም; እሥራኤል 8/10/2011**
8 **_የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች!!_**